## ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ቀንን አስመልክቶ ከኢሰመጉ የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ

ታህሳስ 04/2015 ዓ.ም

ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ቀን በየአመቱ ዲሴምበር 10 በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚከበር ሲሆን የዘንድሮ የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ቀን በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ74ኛ ጊዜ እንዲሁም በሀገር አቀፍ ደረጃ ለ34ኛ ጊዜ « ክብር፣ ነጻነትና ፍትህ ለሁሉም » (dignity, freedom and justice for all ) በሚል መሪ ቃል እየተከበረ ይገኛል፡፡

ኢሰመጉ ላለፉት 31 አመታት ከማንኛውም የፖለቲካ ቡድን፣ ሃይማኖት፣ ብሔር እና ጎሳ ተፅዕኖ ነፃ በመሆን፤ የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መጎልበትን፣ የሕግ የበላይነት መስፈንና የሰብዓዊ መብቶች መከበርን ዓላማ በማድረግ ለሰብዓዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር እየሰራ ይገኛል፡፡

ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ቀን በሚከበርበት በእዚህ ወቅት በተለያዩ የሀገሪቷ ክፍሎች እና አካባቢዎች ውስጥ በተደጋጋሚ ጊዜ በንፁሃንና ራሳቸውን መከላከል በማይችሉ ባልታጠቁ ዜጎች ላይ ግጭቶች እና ጥቃቶች እየተሰፉፉ ይገኛሉ፡፡ በእነዚህም ግጭቶች እና ጥቃቶች ምክንያት በርካታ ሰዎች ህይወታቸውን አጥተዋል፣ የአካል ጉዳት እና ጾታዊ ጥቃቶች ደርሶባቸዋል፣ ለዘመናት ከኖሩበት ቀያቸው ተፈናቅለዋል፣ ቤት ንብረታቸው ወድሟል እንዲሁም ለህገ ወጥ እስርና መሰወር ተዳርገዋል እየተዳረጉም ይገኛሉ፡፡ በመሆኑም ሰብዓዊ መብቶችን አስመልክቶ ዋነኛው ሃላፊነት በመንግስት ላይ የሚጣል ሲሆን መንግስትም በእዚህ መሰረት የዜጎችን መብት የማክበር፣ የማስከበርና የማሟላት ሀላፊነቶች አሉበት፡፡ ነገር ግን እነዚህ ዋነኛ የመንግስት ሀላፊነቶች በአግባቡ እና በበቂ ሁኔታ ባለመፈጸማቸው በሀገሪቱ ያሉ የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታዎች መሻሻሎችን ማሳየት አልቻሉም፡፡ ስለሆነም መንግስት የዜጎችን ሰብዓዊ መብቶች የማክበር የማስከበር እና የማሟላት ሃላፊነቱን እንዲወጣ፣ ግጭት ባለባቸው አካባቢዎች ለተጎዱት ዜጎች አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግና ጥፋተኞችን ለህግ በማቅረብ ለሰብዓዊ መብት መከበር ያለበትን ግዴታ በመወጣት ዜጎቿ በሰላም ወጥተው እንዲገቡ፣ ንብረት ማፍራት እንዲችሉ እና ተከባብሮ የመኖር ባህላችንን በማስቀጠል እውነተኛ የሰብዓዊ መብት የተከበረባት ሀገር በመገንባት ረገድ የበኩሉን እንዲወጣ ከምንጊዜውም በበለጠ መስራት እንደሚኖርበት ኢሰመጉ ያምናል፡፡ በተጨማሪም የሀገር ሽማግሌዎች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የማህበረሰብ አንቂዎች፣ የሲቪል ማህበራት፣ መገናኛ ብዙሃን፣ የሃይማኖት ተቋማት እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በአጠቃላይ ለሰብዓዊ መብቶች መከበር የበኩላችንን አስተዋጽኦ በማድረግ በሰላማዊ ሀገር ግንባታ ሂደቱ ላይ የበኩላችሁን ሃላፊነት እንድትወጡ ኢሰመጉ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

በመጨረሻም ኢሰመጉ በአለም አቀፍ ደረጃ ለ74ኛ ጊዜ እንዲሁም በሀገር አቀፍ ደረጃ ለ34ኛ ጊዜ « ክብር፣ ነጻነትና ፍትህ ለሁሉም » (dignity, freedom and justice for all ) በሚል መሪ ቃል እየተከበረ በሚገኘው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ቀን እንደመሪቃሉ ሁሉ ክብር፣ ነጻነት እና ፍትህ ለሁሉም ሰዎች የምትሰጥ እና ሰብዓዊ መብቶች ከጫፍ እስከ ጫፍ የሚከበሩባት ሀገርን ማየት የምንጊዜም ምኞቱ መሆኑን እና ይህም እስከሚረጋገጥ ጊዜ ድረስ ያለእረፍት እንደሚሰራ ይገልጻል፡፡

አዲስ አበባ ፤ኢትዮጵያ